# ምነው ዲያስፖራ!

ትናንት ለኢህአዴግ- ሲሰራ የነበረውን - "ያን ባለጌ ወራዳ

አላዋቂ ማይም- አጎብዳጅ- ለጠላት ያደረ ክፉ ባንዳ

ትምህርት ቤት ያልረገጠ- ደፋር ማይም- የማያውቀን ዘላባጅ

ህሊናውን የሸጠ- የወራዶች ሁሉ ውራጅ"

ተማረ እንዲባል ለስሙ- በመለስ ቀጭን ትዕዛዝ

እንዲመች ሆኖ- እንዲሰራ- ለወያኔው አገዛዝ



ሲቪል ሰርቪስ ገብቶ

በህግ ተመርቆ ወጥቶ

ለአግአዚ ጦር አለቃ- ሆኖ- በህዳር ሰማይ የጥይት መብረቅ ያጮኸ

እናቶችን በለቅሶ - በደረታቸው ያስዳኸ

ታዬ አሉ ዘንድሮ- እዚህ ዲሲ- አሜሪካ ምድር ገብቶ

"አገር ከድቶ- ከመለስ ተጣልቶ።"

ውሎ ሳያድር- ከተቃዋሚወች ጎራ

ሲቀላቀል ሲያወራ

"ያንን ጠብደል ማይም-ያ ደደብ ያልነውን" ሰው

ይጀመራል ክፍከፋው- ይቀጥላል ምስጋናው

እናም በቆዩት ቦታ- እሱን ከፍ እናደርግና

ሊቅ ያለ እሱ ማን አለ- ብለን እንለውና

ትግሉ በወያኔ- ተመልሶ ሲጠለፍ- እናያለን እንደገና።

ወያኔ በስልቱ- በሚያውቀው ጎዳና

ጠላት አስመስሎ ወዳጁን- ማከላችን ያስገባና

ትግላችንን ሲያኮላሸው- መመዘን አቃተንና

ትግል ትግል እንላለን- ይህም ትግል ተባለና!

ምነው ዲያስፖራ- ምነው ሚናችን ቅጡን አጣ

የወያኔ ደጋፊ ነን- ወይስ ተቃዋሚ ባለአንጣ?

ዳግማዊ ዳዊት፣
Ethio_dagmawi@yahoo.com
ጥቅምት 2003 ዓ.ም.